የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የ ፍ/ብሔር ችሎት ዋና ክፍል

የአከራይ እና ተከራይ ቅርንጫፍ
ሕንፃ B, 510 4th STREET, N.W.፣ ክፍል 110 WASHINGTON, D.C. 20001
ስልክ (202) 879-4879

______________________________ በ ______________________________

______________________________ ______________________________

ከሳሽ *ተከሳሽ*

____________አተቦ (**LTB)**______________

የፍርድ ወሳኔን ለማስፈፀም የሚወጣ የንብረት ማስከበሪያ ትዕዛዝ
(የሰዓት ክፍያዎች፣ ገቢዎች ፣ ደሞዞች፣ ኮሚሽኖች እና ጡረታዎች) ላይ እንዲቆረጥ ("ጋርኒሺንግ") ማድረግ

ለ፡ ______________________________ ቆራጭ

በ ______________________________ ተከሳሹ $ ______________ በዓመት ________ ወለድ ጋር ከ ______________________________ ጀምሮ እንዲከፈል እና $ ______________ ኪሳራ ታስቦና ለተከሳሽ የሚከፈል ካለ ተቀንሶ ፣ ይኽ ማስከበሪያ በወጣበት ቀን የሚመጣውን ጠቀላላ የገንዘብ መጠን $ ______________ በተከሳሽ ላይ የፍርድ ወሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ

ማሰታወሻ: ይኽንን የገንዘብ መጠን ወደፊት የሚጠራቀም ወለድ ከፍ የሚያደርገው ሲሆን በፍርዱ መክንያት የሚከሰቱ ተጨማሪ ወጭዎች ተጠራቅመው በኋላ ላይ ጠቀላላ መጠኑን ከፍ ሊያደርጉት ይችላሉ። ከዚህ ማስከበርያ ውጭ የተክፍሉ ክፍያዎችም ጠቅላላውን የገንዘብ መጠን ሊቀንሱትም ይችላሉ። ማናቸውንም የተጣራ ገቢ ቆርጦ ማስቀረት ከማቆምዎ በፊት በፍርድ ውሳኔው መሰረት መከፈል የሚገባው ሙሉ በሙሉ መከፈሉን ለማረጋገጥ ከከሳሹ ወይም ከጠበቃው ጋር ግንኙነት ያድርጉ።

ይኽ የንብረት ማስከበሪያ ትዕዛዝ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ለተከሳሹ ለመከፈል የደረሰ ወይም የሚከፈል የተጣራ ገቢ ላይ የተጣለውን የገንዘብ መጠን ወይም በሕግ የተበየነውን በተመለከተ (መመሪያ 1-3 ን ይመልከቱ) መያዣ ሆኖ ቀጣይነት ያለው ተቆራጭነትን የሚያስከትል መሆኑን በዚሁ እሳውቀንዎታል።

ከማንኛውም የስራ ሳምንት ወይም ሌላ የክፍያ ጊዜ የተክሳሹ የተጣራ ክፍያ ላይ (መመሪያዎች 1-2 ን ይመልከቱ) ከዚህ በታች ከሰፈረው **አነስተኛውን** ቆርጠው እንዲያስቀሩ በዚህ ማስከበሪያ ታዘዋል:

(1) ከያንዳንዱ የሥራ ሳምንት ወይም የክፍያ ጊዜ የተከሳሹ የተጣራ ገቢ ላይ 25%፣ ***ወይም***

(2) የሱ(ሷ) ሳምንታዊ ክፍያ፣ ክፍያው በሚፈፀምበት ወቅት ለው የፌዴራል ዝቅተኛ የሰዓት ክፍያ በ 30 ጊዜ ተባዝቶ ከሚገኘው ውጤት በልጦ የሚገኘው መጠን። ከሳምንት የክፍያ ጊዜ የተለየ ሌላ የክፍያ ጊዜን በተመለከተ ደግሞ መጀመሪያ ክፍያው በሚፈፀምበት ወቅት ያለውን የፌዴራል ዝቀተኛ የሰዓት ክፍያ በ 30 ያባዙ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ ያገኙትን ውጤት ሂሳቡ በሚሰላበት የክፍያ ጊዜ ውስጥ ባሉት ሙሉ እና/ወይም ከፊል ሳምንታት አባዘተው የሚገኘውን መጠን (መመሪያ 1-2 ን ይመልከቱ) እና

በያንዳንዱ የ"ካሌንዳር" ወር ከሚያልቀው ከተከሳሹ የመጨረሻ የክፍያ ጊዜ አንስቶ በ 15 ቀናት ውስጥ፣ ወለድ፣ ኪሳራ እና ሌሎችንም ወጭዎች ጨምሮ በፍርዱ የተወሰነው የገንዘብ መጠን ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ለ ______________________________ ይከፈሉ።

ለአሰሪ - ቆራጭ ማስታወቂያ: ይኽ ማዘዣ በደረሰዎ በአስር (10) ቀናት ወሰጥ ከዚህ በታች የሚከተሉትን መጠይቆች፣ የሃሰት ቃል መስጠት በሕግ የሚያሰቀጣ መሆኑን አውቀው፣ መመለስ እና መልሶችዎ የሰፈሩበትን የዚህን ወረቅት ግልባጭ (ኮፒ) ፍ/ቤቱ ዘንድ ፋይል ማድረግ እና በፖስታ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ለከሳሽ እንዲደርስ ማድረግ የጠበቅብዎታል። ይኽን ሳያደርጉ ቢቀሩ ክሳሹ ክስ ላቀረበበት የገንዘብ መጠን በሙሉ ከውለድ እና ከኪሳራ ጋር እንዲከፈሉ ሊወሰንብዎት ይችላል።

የፍ/ቤት ፀሐፊ

____
የከሳሽ ጠበቃ

አደራሻ:______________________________ በ: ______________________________

ምክትል ፀሐፊ

ስልክ ቁ . *ትዕዛዙ ወጪ የተደረገበት ቀን:*

በአሰሪው/ ቆራጭ ("ጋርኒሺ") መመልስ ያለባችው መጠይቆች

1. ተከሳሹ የርስዎ ሰራተኛ ከሆነ በህግ ብያኔ ሊቃሉ በተሰጠው ትርጉም መሰረት (መመሪያ 1 ን ይመልከቱ) ፣ ሰራተኛው የሚያገኘውን የተጣራ ክፍያ እና የሚከፈልበትን ቀን ያስፈሩ። በተጨማሪም የማህበርዊ ዋስትና ቁጥሩን ("ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር") ያስፈሩ።Also state his Social Security Number.

መልስ: ______________________________

____

(ከጀርባ ይመልከቱ)

2. ተከሳሹ ባሁኑ ጊዜ እርስዎ ዘንድ እየሰራ ካልሆነ ፣ ይኸ የማስከበሪያ ተዕዛዝ ከደረስዎ ቀን ቀደም ብለው ባሉት አራት ውራት ወሰጥ እርስዎ ዘንድ የይሰራ ነበር? ከነበር መቼ ነው የሚሰጠው አገልግሎት እንዲቋረጥ የተደረገው?

መልስ: ______________________________

3. ቀደም ብሎ እንዲደርስዎ በተደረገ የንብረት ማስከበሪያ ተዕዛዝ መሰረት ዕዳ እንዲከፈል ከዚህ ተከሳሽ ክፍያዎች ወይም ገቢዎች ላይ ባሁኑ ወቅት እየቆረጡ ከሆነ ከፍያውን የሚከፍሉትን የፍ/ባለመብት ስም እና የንብረት ማስከበሪያ የታዘዘበትን ክስ የመዝገብ ቁጥር ያስፍሩ።.

መልስ: ______________________________

4. የተከሳሹ ቅጥር በ ______________________ እንዲቋረጥ ተደርጓል።

ሀሰተኛ ቃል ብሰጥ የሚደርስበኝን ህጋዊ ቀጣት አውቄ ከዚህ በላይ ለሰፈሩት መጥይቆች የሰጧኋቸው መልሶች፣ ማናችውንም መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮቹን በሚመለከት፣ እስከማውቀው እና እስከማምነው ድረስ እወነተ እና ተክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ።

ቀን: ______________________________

አሰሪ -ቆራጭ (“ጋርኒሺ”)

ለአሰሪና ለቆራጭ (“ጋርኒሺ”) መመሪያ

1(ሀ) ክፍያ (“ዌጅስ”) ማለት ክፍያም ይሁን ደሞዝ፣ ኮሚሽን፣ ጉርሻ (“ቦነስ”) ወይም በሌላ ስም የተሰየመ ይሁን አይሁን ለማንኛውምልትሰጠ አገልግሎት የተከፈልን ክፍያ የሚያካትት ሲሆን በጡረታ “ሪታየርሜንት” መርሐ ግብሮች መሰረት የሚደረጉ ክፍያዎችን ያካተታል። (ለ) “የተጣራ ክፍያ” ማለት ማንኛውም በህግ መሰረት ተቀናሽ መደረግ ያለበት ከተቀነስ በኋላ የሚቀረው የአንድ ሰው ገቢ ማለት ነው።

2. “ዝቅተኛው የፌዴራል የሰዓት ክፍያ” ማለት በ Sec. 6(a)(1) of the Labour Standards act of 1938 (29 U>S.C. § 206 (a)(1) መሰረት የተደነገገው ከፍተኛው የፌዴራል ዝቅተኛ የሰዓት ክፍያ ማለት ነው። ከመስከረም (“ሴፐተምበር”) 1፣ 1997 ጀምሮ ይኸ ክፍያ በሰዓት $ 5.15 ነው። ከዚያ በኋላ ባነስተኛው የፌዴራል የሰዓት ክፍያ ላይ ለሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ቆራጩ (“ጋርኒስሺው”) ተገዢ መሆን አለበት።

ከ ታህሳስ (“ዲሰምበር”) 17፣ 1971 ጀምሮ የፀደቀው እና ፀንቶ ሰራ ላይ የዋለው የ “ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ Consumer Credit Protection Act of 1971” ከዚህ ቀድሞ ይደረግ የነበረውን ካልተጣራ ክፍያ ላይ በፍ/ባለመብቱ ሰራተኛ ላይ የተወሰነበትን መቶኛ ክፍያ የመቁረጥ ዘዴ ያስቀራል። ከሐምሌ (“ጁላይ”) 1፣ 1971 ጀምሮ የፀናው የ “Federal Consumer Protection Act (Title III)” ድንጋጌ ወሰጥ መቁርጥን በሚመለከት የተቀመጡትን ገደቦች በመውሰድ ለማንኛውም የስራ ሳምንት ወይም ለሌላ ማንኛውም ጊዜ የተጠረቃቀሙ የተጣሩ ከፈያዎች ላይ በቀጥታ ተፈፃሚ የሚሆን የ”ኤክዘምሽን” ፎርሙላ ይደነግጋል። በ “ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ኮሚሽነር” ደንቦች መሰረት፣ ከሁለቱ አማራጭ የአቆራረጥ ፎርሙላዎች መካከል የትኛው ውደ አነስተኛ ተቆራጭ እንደሚያመራ ለመወሰን (የዚህን ትዕዛዝ የግምባር ገፅ ይመልከቱ)፣ 1) 25 % ኛው የፎርሙላው ክፍል በሚመለከተው አጠቃላይ የክፈያ ጊዜ የተጠረቃቀሙት (“አግረጌት”) ክፍያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣ (2) የፎርሙላው የፌዴራል አነስተኛው የሰዓት ክፍያ (ይኸው የፌደራል አነስተኛ የሰዓት ክፍያ 5.15 እስከሆነ ድረስ) በሚከተለው መልክ ይሰላል፡ ለ 2 ሳምንት የክፍያ ጊዜ- 2 x 30 x $5.15= $309.00፣ በወር ሁለቴ ለሚፈፀም የክፍያ ጊዜ- 2 1/6 x 30 x 5.15= $669.45።

3. ይኸ የንብረት ማስከበሪያ ትዕዛዝ፣ ምክንያቱ በሆነው ፍርድ መሰረት ከከዚህ በላይ በተበየነው መሰረት የተጣራ ገቢ በሚባለው ላይ መያዣ በመሆን በቀጣይ እንዲሁም በተከታታይ እየተቆረጠ የተወሰነው ገንዘብ በሙሉ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል።

4. ተከሳሹ ለ 90 ቀናትት ወይም በታች እርስዎ ዘንድ ያለውን ስራውን አቋርጦ እንደገና ስራውን እንዲቀጥል ቢደረግ እንኳ ይኸ የንብረት ማሰከበሪያ ሙሉ በሙሉ የፀና እና ተግባራዊነቱ ቀጣይ ሆኖ ይቆያል። ስለሆነም እርስዎ ከተጣራው ገቢው ላይ እየቆረጡ ማስቀረት የጠበቅብዎታል።

5. ተከሳሹ ለ 90 ቀናትት ወይም በላይ እርስዎ ዘንድ ያለውን ስራውን ቢያቋርጥ፣ ይኸም ማስከበሪያ ይቋረጣል። ስለሆነም እርስዎ፣ የተቋረጠበትን ቀን እዚህ ላይ በተተወው ክፈት ቦታ ላይ በማስፈር የማስከበሪያውን ግልባጭ (ኮፒ) ለፍ/ቤቱ ይመልሳሉ።

6. በዚሁ ተከሳሽ ላይ ሌሎች የፍርድ ማስከበሪያዎች እንዲደርስዎት ተደርጎ ክሆነ እና ገና መከፈል የሚገባቸ ገንዘቦች ያልተቆረጡ ከሆነ፣ እንደአደራረሳቸው ቀድም ተከተል የተወሰኑትን የገንዘብ መጠኖች ማስከበሪያው የሚያዘው እስኪሟላ ድረስ መቁረጥ ይጠበቅብዎታል። በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም በላይ ማስከበሪያዎች ከደረሱዎት፣ ቅድሞ የ “ዩናይትድ ስቴትስ ማርሻል” ማህተም የሰፈረበት፣ ብመጀመሪያ የመፈፅም ቀድሚያ አለው።

7. ተከሳሹን በሚመለከት ቀደም ብለው በደረሱዎት ማንኛቸውም ክሶች ወይም የፍርድ ወሳኔዎች መሰረት መቆረጥ የሚገባቸው ተቆርጠው ሳያልቁ ይኸንኛውን ማስከበሪያ ለማሰፈፀም ማንኛውንም የተጣራ ክፍያ መክፈል ወይም ቆርጠው ማስቀረት የለብዎትም። ያን ጊዜ ግን በዚኸኛው ማስከበሪያ ተሰልቶ የሰፈረውን የገንዘብ መጠን ከተጣራ ከፈያው ላይ ቆርጠው መክፈል የጠበቀብዎታል። ይኸ ማሰከበሪያ ለመፈፀም እየጥበቀ ወይም እየተፈፀመ ባለበት ጊዜ ተካሳሹ ስራውን ለቅቆ ቢሄድ ከላይ በተራ ቁ 4 እና 5 የሰፈሩትን መመሪያዎች ይመልከቱ።

ማስጠንቀቂያ የ “D.C. CONSUMER CREDIT PROTECTION ACT OF 1971 (P.L. 92-200) ክፍል. 6 አንድ አሰሪ፣ ገና ለተከሳሹ ካልተከፈሉ ገቢዎቹ ላይ የፍርድ ወሳኔ ለማሰፈፀም መቁረጥ በመጀመሩ ወይም እንዲቆረጥ እየተሞከረ በመሆኑ ምክንያት አንድን ሰራተኛ እንዳያሰናብት ይከለክላል። ፍርድን ለማስፈፀም የሚደረግ ከክፍያ ላይ የመቁረጥ ጉዳይ የሚመለከተው የፌዴራል ሕግ፣ የሰራተኛው ክፍያዎች ለፍርድ ማስፈፀም ተቆራጭ እንዲሆኑ በተደርገበት ሁኔታ እንዲህ ዓይንት ስንብት መስጠትን የሚከለክል ሲሆን፣ ይኸንነው ህግ ሆን ብሎ የጣሰ አሰሪ ከ $1000.00 ባልበለጠ መቀጫ ወይም ከአንድ ዐመት ባልበለጠ እሥራት ወይም በሁለቱም ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል።

Translated by JTG, inc. 01/2017